# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 307 መጋቢት 19 2006


**የወያኔ ጉጅሌ ሆን ብሎ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እንዲጋጩ፣ እርስበርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩና እንዲፈራሩ ለማድረግ የሚያደርገውን ጥረት ድርጊቱ በእሳት መጫወት መሆኑን አውቆ ከዚህ እኩይ ተግባር እንዲታቀብ ግንቦት 7 እያሳሰበ በማንኛውም ሁኔታ በማህበረሰቦች መካከል ለሚደርስ ግጭትና ጉዳት ሙሉ ሀላፊነቱ የወያኔና የወያኔ ብቻ መሆኑን አጥብቆ ያስገነዝባል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዬው የህዝብ ቁጣ ገንፍሎ ለመውጣት መቃረቡ በምሁራን ዘንድ እየተነገረ ነው

የህዝቡ ምሬት ከሚገባው በላይ ጨምሩአል ያሉት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው በርካታ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር የህዝቡ ቁጣ መፈንዳቱ አይቀሬ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ደርግን የተካው ጉጅሌው ወያኔ ትምህርት ወስዶ የተሻለ ስርዓት ይገነባል ተብሎ ቢጠበቅም፣ እሱም የለየለት አምባገነንና አፋኝ ስርዓት ለመሆን ከመብቃቱም በላይ፣ ጭቆና እንዲወገድ፣ እኩልነት እንዲረጋገጥ ከመስራት ይልቅ ጥላቻና አምባገነንነት የአገዛዙ የአመራር ዘይቤ ሆኖአል ሲሉ አገዛዙን ወቅሰዋል።

የሕዝብን ጥያቄ በሰላይ ጋጋታና በወታደር ብዛት ማዘግየት እንጂ መጨፍለቅ በፍፁም አይቻልም። በጥላቻና በሸብር የተሞላ መርዘኛ የሆነ ፕሮፓጋንዳ መስበክ፤ ማሰፈራራትና ወዮልህ ማለት መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል የሚገልፁት እኒሁ ምሁራን ፤ በኑሮ ውድነትና በመልካም አሰተዳደር ዕጦት የተማረረው ህዝብ በቱኒሲያ፤ በግብፅና ዩክሬን የታየውን አይነት ህዝባዊ አመፅ አያደርግም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው ሲሉ እምነታቸውን አስቀምጠዋል። የጉጅሌው ወያኔ የሕዝብን የለውጥ ፍላጎት በስለላና በጦር ኃይል እጨፈልቃለሁ የሚል አምባገነናዊ አካሄዱ የቁልቁል ጉዞ እንደሚወስደው የሚጠቅሱት ምሁራኑ፣ ወያኔ እየተንደረደረ እየሄደበት ያለው የመቀመቅ ጉዞ፣ ሀገርን አይጠቅምምና ሃይ ሊባል ይገባል ሲል ምክርን ለግሰዋል።

በመጨረሻም የጉጅሌው ወያኔ ሟርተኛ ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን የሚያሸብርና ወደ ደም መቃባት የሚወሰድ የእልህ ጉዞ መሆኑን በመጠቆም፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገራችን ካለችበት የፖለቲካ አዙሪት አንድትወጣ ከፍርሃት ራሳችንን አውጥተን እጅ ለእጅ ተያይዘን ለነፃነትና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል እናግዝ ሲል ወገናዊ ምክራቸውን አሰምተዋል።

## ጉጅሌው ወያኔ ከወደ ኦሮሚያዋ አምቦ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆችን ማፈናቀል መጀመሩና ንፁሃን ዜጎችን ማዋከብና ማሰሩን እንደቀጠለ ተሰማ

ተፈናቃዮቹ በምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ዳኖ ወረዳ ውስጥ ከ 20 አመት በላይ የኖሩ፤ በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን በዛቻ ታጅቦ በተደጋጋሚ ይነገራቸው የነበረው ክልላችንን ለቅቃችሁ ውጡ የሚል ማስፈራሪያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወደ ግድያ፤ ድብደባና ወከባ በማደጉ አካባቢያቸውን ጥለው መሸሻቸው ታውቋል።

ተፈናቃዮቹ በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት መንገሱን በመግለጽ እስካሁን ከ26 በላይ ሰዎች በፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ሚሊሺያዎች በአደባባይ ድብደባ እንደደረሰባቸውና እጅና እግራቸው እንደተሰበረ ያጋለጡ ሲሆን አቶ ጌጡ ክብረት የተባለ ግለሰብ በገበያ ቦታ በገጀራ ተቆራርጦ ህይወቱ ማለፉንም ተናግረዋል። ሰሚ ያጡት እኒሁ ተፈናቃዩች ወደ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ጽ/ቤት በመምጣት ‹‹ፍትህ እንድናገኝ ለኢትዩጵያ ህዝብ ሰቆቃችንን አሰሙልን በማለት መማጽናቸውን ዘጋቢያችን አድርሶናል፡፡

በሌላ ዜና ፋሽስቱ ወያኔ በመላ ሃገሪቱ ንፁሃን ዜጎችን ማዋከቡና ማሰሩን እንደቀጠለ መሆኑ ተሰምቷል።

በምእራብ ጎጃም ዞን በሜጫ ወረዳ በእናሽንፋለን ቀበሌ ለአበባ ምርት በሚል የከርሰ ምድር ውሃ ለማውጣት ፋሽስቱ ወያኔ እንቅስቃሴ መጀመሩን የተቃወሙ ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሆኑ አርሶ አደሮች፣ ሴቶችና ወጣቶች በገፍ ተይዘው በመርዓዊ ከተማ እና በዱርቤቴ እስር ቤቶች መታሰራቸውንና ከፍተኛ እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የአፍሪካ ቀንድ የሰብአዊ መብት ሊግ ባወጣው መግለጫ ደግሞ በደቡብ ኦሮምያ በጉጂ ዞን በሻኪሶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ቁጥራቸው 200 የሚጠጉ ተማሪዎች በአዶላ ከተማ መታሰራቸውን አጋልጧል። ብዙዎቹ ወጣቶች ከጸጥታ ሃይሎች በተተኮሰ ጥይት እና ድብደባ መቁሰላቸውን ሊጉ ገልጿል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የቀድሞው የኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ዓለማየሁ አቶምሳ በሕወሃት ሲሰልል እንደነበር ተጋለጠ

ዓለማቀፍ ህግን በጣሰ መልኩ የግል መረጃዎችን ሳይቀር ለመበርበር የሚያስችል ፊን ፊሸር የተሰኘ ሶፍት ዎር ከእንግሊዝ ኩባንያዎች በከፍተኛ ውጭ ምንዛሪ በመግዛት በግንቦት 7 እና ከፍተኛ አመራር አባሎቹ ላይ ስለላ ሲያከናውን እንደነበር የተደረሰበትና ባሁኑ ሰአት ጉዳዩ በዓለማቀፍ ደረጃ በክስ ሂደት እየታየበት ያለው ሕወሃት በሀገር ውስጥም ታማኝ በሚባሉት ከፍተኛ ባለስልጣኖቹ ላይ ሳይቀር በተግባር ላይ እያዋለው መሆኑን ምንጮቻችን ጠቆሙ።

በተለይ በቅርቡ በሞት ለተለየው የኦሮሚያው ፕሬዚዳንትና የወያኔው የቁርጥ ሰው ዓለማየሁ አቶምሳ ቅርብ እንደሆኑ የጠቆሙት ምንጮቻችን እንዳጋለጡት ከሆነ ሟቹ በከፍተኛ የህወሃት ስለላ ስር እንደነበር ሳይደብቁ ተናግረዋል። ከቅርብ የቤተሰብ አባላት ጋር ሳይቀር የሚጻጻፋቸው የኢሜል መልክቶችና ሌሎችም ቀድመው ይነበባሉ ብሎ ይገምት እንደነበር እንዳወራላቸው የተቆሙት ምንጮቻችን የግል ጋደኞቹ ያልጻፏቸው ነገር ግን በነሱ ስም እንደተጻፉ ተደርገው የደረሱት ብዙ መልክቶች እንደነበሩም እንደነገራቸው አጋልጠዋል። አመራጭ የለኝም በማለት ብዙ ጊዜ ይናገር እንደነበር የሚአትቱት እኒሁ ምንጮቻችን ለሟቹ የደረሰው አይነት ተመሳሳይ መንፈስ ያላቸው መልክቶች ለሌሎችም ጉደኞቹ እንደተላከላቸው እንደሚያውቅ እንደነገራቸው አስረድተዋል።

ከዚህ በፊት በወያኔ የስልጣን ኮርቻ ላይ የነበሩና የሚጠረጥራቸውን ባለስልጣናቱን ከስራቸው ሰዎችን በበመደብ ይከታተል እንደነበር የሚጠቁሙት ምንጮች አሁን ግን በተለይ ፊን ፊሸር የተባለውን ሶፍት ዌር በስራ ላይ ካዋለ ወዲህ ስካይፒና ሌሎች ኢንተርኔትን መሰረት ያደረጉ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰሙትንና የተናገሩትን ሳይቀር ማን ምን እንዳደረገና እንደተጻጻፈ፣ በመለቃቀም ምናልባት እነዚህ ሰዎች ወደፊት ችግር ቢፈጥሩ በማስረጃነት ለማቅረብ በመረጃነት በማሰባሰብ ላይ እንደሆነ ተጠቁሟል።

በአዲስ አበባና በሌሎችም ታላላቅ ከተሞች የተቀነባበሩ የቦንብ ፍንዳታዎችን በንጹሃን ዜጎቻችን ላይ በማፈንዳት ሌሎችን በሀሰት መወንጀሉ ባንዳንድ ዓለማቀፍ ሚዲያዎች የተጋለጠበት ፋሽስት ወያኔ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ ሕዝባዊ ተቋማትን በድጋሚ የማፈራረስ እቅዱን እያጠናቀቀ እንደሆነ ተጠቆመ

ሕወሃት መራሹ አገዛዝ ራሱ ከፈጠራቸው ወይም መቶ በመቶ ከሚቆጣጠራቸው ሃይማኖታዊም ሆነ ሕዝባዊ ተቋማት በቀር ለሌሎች ቦታ እንደሌለውና ፈጽሞ ሊያጠፋቸው የመጨረሻውን እርምጃ ለመውሰድ እየተጠናቀቀ ባለ እቅድ ላይ መሆኑ ተጠቆመ። ወትሮም የይስሙላ ዴሞክራሲውን እንዲሸፍኑለት በማለት በስመ ነጻ ተቋም እንዲደራጁ እንጅ ራሳቸውን ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ከመሰረቱ ፍላጎት እንደሌለው የሚነገርለትና ራሱም በቁጥር የሚበዙ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ ተቋማትን አፋኝ ሕጎችን በማውጣት የዘጋው ሕወሃት አሁን ግን ፊት ለፊት የሽብርተኝነትንና አክራሪነትን መፈክር እያቅራራ ከጫወታ ውጭ ሊያደርጋቸው እንደሆነ የደረሰን መረጃ ይጠቁማል።

ባሁኑ የሕወሃት አፍራሽ እርምጃ ከጫወታ ውጭ የመሆን ተራ የሱ እንደሆነ በሰፊው የሚነገርለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የተቋቋመው ማሕበረ ቅዱሳን የሚባለው ሃይማኖታዊ ተቋም ሲሆን ይህን ሃይማኖታዊ ተቋም እንዳልነበር አድርጎ ለማጥፋት አልያም የጎላ እንቅስቃሴ በማያደርግበት ደረጃ ለመሰባበር ከፍተኛ ስራ እንደተሰራና ተግባራዊ እንቅስቃሴውንም ለመጀመር ሕወሃት መራሹ ሃይል ከመጨረሻው ምእራፍ ላይ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ጠቁመዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የምንሰጠዉ መሬት ስለሌለን የገጠሩ ወጣት እየተሰደደ ነዉ አለ

የገዢዉ ፓርቲ የኢህአዴግ የ6 ወራት የስራ አፈፃፀም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት አዳራሽ በተገመገመበት ወቅት ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ለወጣት አርሶ አደሮች የምንሰጠዉ መሬት ባለመኖሩ መሬት ኖሮት ስራ ላይ ከተሰማራዉ ወጣጥ የተሰደደዉ ወጣት ይበልጣል ሲል መናገሩን ከወደ አገር ቤት የደረሰን ዜና ያስረዳል። ስራ ፈጠራውም ሆነ ሳይታረሱ የኖሩትን ወል መሬቶችን እያደራጁ ለወጣቱ አርሶ አደር መስጠት አላዋጣም ያለዉ ሃይለ ማርያም ፤ በገጠር መሬት የማከፋፈል ስራ ከተሰራ በኋላም ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔን ከፋፋይ አገዛዝ እናምክን

የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ሊከበርላቸውና ሊያሳድጋቸው የሚገቡ የተለያዩ የባህልና የታሪክ ቅርሶች ያሏቸውን ያህል በብዙ መንገድ የሚያይዝ የጋራ ታሪክ ቅርስና ዝምድና አላቸው። ልዩነቶቹ ራሳቸው ተጠቃቃሚ ለሆነ የእርስበርስ ግንኙነታቸው ጠቃሚ እንጂ ከአንድ ሀገር ማህበረሰብነታቸውና ከጋራ ህልማቸው ጋር የሚጋጩ የጠብና የግጭት መንስኤዎች አይደሉም። ከጠብና ግጭት ማንኛውም ብሄር ብሄረሰብ ተጠቃሚ አይደለም። ከጠብና ግጭት ጥቅም ይገኛል ብለው የሚያስቡ "ግርግር ለሌባ ይመቻል" የሚለውን የወሮ በላ ፍልስፍና የሚከተሉ የቀን ጅቦች እንጂ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች አይደሉም። በወያኔ የግዛት ዘመን የደረሱትን ግጭቶች መፈናቅሎችና የተፈጠሩትን የእርስበርስ ጥርጣሬዎችን ልብ ብሎ ለተመለከተ ሁሉም በአገዛዙ እና በሎሌ የበታች ሹማምንቱ የተፈጠሩ እንጂ አንድም ጊዜ እንኳን ከህዝብ የመነጩ አይደሉም።

የወያኔ ጉጅሌ በአገዛዝ ዘመኑ ሁሉ ብሄር ብሄረሰቦችን ከሚያይዟቸው የጋራ ማህበራዊ ቅርሶችና ህልሞች ይልቅ ካለመታከት ልዩነቶቻችን ላይ ያተኮረ ፖለቲካ እያካሄደ እንዳለ ግልጽ ነው። ከዚህ አልፎም አዳዲስ የእርስበርስ ግጭቶችን እና ጠቦች እንዲፈጠሩ ተግቶ የሚሰራ ከፋፋይ ቡድን ነው። እርስበርሱ መጠራጠርና መፈራራት እንዲሰፍን ልዩ ልዩ ስልቶችን ይቀይሳል። ከአንዱ ብሄረሰብ ተንኳሽ አዘጋጅቶ ሌላው ብሄረሰብ ላይ አደጋ እንዲደርስ ከዚያም ተጠቃሁ የሚለው አጸፋ እንዲመልስ ያደርጋል። የአንዱን ብሄረሰብ መንደርና ንeበረት በእሳት ለኩሶ በሌላው ብሄረሰብ እንዲመካኝ ያድርጋል። አንዱ በአንዱ ላይ እንዲያማርር ከንፈሩን እንዲነክስ ማድረግ ለወያኔ ጉጅሌዎችና ለሎሌዎቻቸው እንደፖለቲካ ጥበብ ከታየ ሁለት አስርት አመታት አልፈዋል። በየትኛውም የሀገራችን አካባቢዎች የተቀሰቀሱ የርስበርስ ጥርጣሬዎችና ግጭቶችን ያሸተተ ሁሉ ወያኔ፣ ወያኔ እንደሚገሙ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው።

ወያኔዎች የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ከፋፍለውና ከቻሉም አጋጭተው ካልሆነ በስተቀር የዝርፊያ ኢኮኖሚያቸውን መቀጠል እንደማይችሉ አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የጋራ ጥቅማቸውንና ህልማቸውን ይዘው የተነሱ እለት ወያኔ ያከተመለት መሆኑን ያውቃል። ለዚህም ነው በየክልሉ እና ዞኑ በፍጹም ከሆዳቸውና ጥቅማቸው በላይ ማሰብ የማይችሉ ግለሰቦችን ከየብሄረሰቡ እየመረጠ የሚሾምልን። ወያኔ ነጻ የህዝብ ምርጫ የሚፈራው ለዚህ ማረጋገጫ ነው፡፡

የወያኔ ጉጅሌዎች ከጊዚያዊ ጥቅም በዘለለ ማሰብ ስለተሳናቸው እንጂ ይህ አካሄዳቸው ለራሳቸውም ለዘለቄታው የማይጠቅም መሆኑን ዘንግተውታል። በልዩነታችን ላይ መጫወት ማለት በእሳት እንደ መጫወት የማይመስላቸው ለዚህም ነው። ይህ የተጀመረው እሳት ራሳቸውንም አይምርም።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ መላው የኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች የጋራ ግብና የተሻለው የነገ ነጻነት ተስፋቸው የሚረጋገጠው በጋራና እጅ ለእጅ ተያይዘው በሚያደርጉት ትግል ብቻ ነው ብሎ ያምናል። ለዚህ የወያኔ መሰሪ የከፋፍለህና አጋጭተህ ግዛ ተንኮል ራሳችንን እንዳናመቻች የገዛ መከራችንን ማራዘሚያ እድል ለዘራፊ ገዥዎቻችን እንዳንሰጥና ለጋራ ህልማችን እንድንቆም ጥሪውን ያቀርባል።

የወያኔ ጉጅሌ ሆን ብሎ በቀጥታና በተዘዋዋሪ  የኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እንዲጋጩ፣ እርስበርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩና እንዲፈራሩ ለማድረግ የሚያደርገውን ጥረት ድርጊቱ በእሳት መጫወት መሆኑን አውቆ ከዚህ እኩይ ተግባር እንዲታቀብ ግንቦት 7 እያሳሰበ በማንኛውም ሁኔታ በማህበረሰቦች መካከል ለሚደርስ ግጭትና ጉዳት ሙሉ ሀላፊነቱ የወያኔና የወያኔ ብቻ መሆኑን አጥብቆ ያስገነዝባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የምንሰጠዉ መሬት ስለሌለን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ቢሆን የምንሰጠው መሬት በማጣታችን ስራ ካገኘው ይልቅ የተሰደደው ወጣት ይበልጣል ብሏል፡፡ ኢህአዴግ ለገበሬዉ የቆመ ፓርቲ ነዉ ብለዉ ሲመጻደቁ የነበሩት ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ተናገሩት ቃል መሬት ጠብ ሳይል ለገበሬዉ የምንሰጠዉ መሬት የለንም ማለታቸዉ ብዙዎችን ግራ ያጋባ ጉዳይ ሆኗል። በተለይ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የዛሬ ሁለት አመት እንደዛሬዉ የማይነጋ መስሎት ለአንድ የህንድ ተሌቪዥን ጣቢያ እጅግ በጣም ብዙ መሬት አለን ባለበት አፉ ዛሬ ለወጣቱ የምንሰጠዉ መሬት የለም ማለቱ የአገዛዙ ባለስልጣኖች የሚናገሩት አፋቸዉ እንዳመጣ መሆኑን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ለአገሩ ወጣቶች የለም ያለዉን መሬት ለህንድ፣ ለቻይናና ለሳዑዲ ቱጃሮች መስጠጡ ወያኔ የቆመዉ ለኢትዮጵያዉያን ጥቅም አለመሆኑን በግልጽ ያሳያል።

አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በንግግራቸው፡ በአማራ ክልል የሚታየው የገጠር ወጣቶች የእርስ በርስ ግድያ አህዝ መጨመር፣ የደቡብ እና የኦሮሞ ክልሎች ወጣቶች በገፍ መስደድ ፣ የጋምቤላ ክልል ወጣቶች ኢትዮጵያዊነታቸውን እየተው ደቡብ ሱዳናዊ ነን ማለት መጀመራቸውና ኢትዩጵያን እየተው ወደ ደቡብ ሱዳን መሄዳቸው፣ የኢትዩጵያ ሶማሌዎች ከአገራቸው ይልቅ ለመቋዲሾ ለመገበር ፍላጎት ማሳየታቸው፣ በመሬት እጦት እና መሰረት ባልያዘው የገጠር ወጣቶችን የስራ ፈጠራ መዳከም የመጣ ነው ሲሉ ገልጸዋል። አቶ ሃይለማርያም ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ምንም አይነት የተቃውሞም ሆነ የድጋፍ አስተያየት አልተሰጠበትም። በስብብሰባው ላይ የተሳተፉ አንድ የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ስር የሰደደው የመልካም አስተዳደር ችግር፣ ሙስና፣ ድህነትና ተስፋ ማጣት ከመሬትና ከስራ እድል ፈጠራ መዳከም በተጨማሪ ለወጣቱ መሰደድ ምክንያት መሆናቸውን አቶ ሃይለማርያም ለማንሳት ሳይፈልጉ ቀርተዋል ብለዋል።

በጥቃቅን እና አነሰተኛ የስራ እድል ፈጠራ እስካሁን ድረስ ሪፖርት የሚደረገው በእጅጉ የተጋነነ ነው ያሉት አቶ ሃይለማርያም ፣ በወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ በየአመቱ ሪፖርት ከሚደረገው በሚልየን ከሚቆጠረው ህዝብ ሩብ ያክሉ ስራ አለመያዙን ገልጸዋል፡፡ ስራ የያዙ ወጣቶችን በተመለከተ ከታች መስሪያ ቤቶች ሪፖርቶች ሲላኩ ቁጥሩ በ5 እንደሚባዛ አቶ ሃይለማርያም አልሸሸጉም።

"በወረዳ እና በክልል ደረጃ የሚገኙ የወጣት፣ የሴቶች እና ህፃናት መስሪያ ቤቶች አንዱን ወጣት አደራጀነው፣ የስራ እድል ፈጠርንለት ብለው ሪፖርት ይልካሉ፣ እንደገና ቴክኒክ እና ሙያ ፤ ጥቃቅን እና አነስተኛ ፤ የሴቶች ሊገ ፤ የወጣቶች ሊግ፤ ፌደሬሺን ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያንን ወጣት በአንድ ቀን ስብሰባ ስላገኙት ብቻ መልሰው በስራ እድል ፈጠራና በተደረጁ ወጣቶች ስም ሪፖርት ይልካሉ፣ ስለ አንዱ ነፍስ ደርበው ደራርበው ሪፖርት በመላክ አንድ ሰው ከአምስት ጊዜ በላይ ተቆጥሮ ሪፖርት እየተደረገ" ነው ያሉት አቶ ሃይለማርያም፣ በወረዳው ነበራዊ ሁኔታ ሲታይ ያ ሪፖርት የሚደረግበት ወጣት በቦታው የለም" ሲሉ አክለዋል። "ይህ ኪሳራ በምንም ሁኔታ ለሚዲያ ሳይወጣ የምክር ቤት አባላት ሊያውቁት ይገባል" ሲሉ አቶ ሃይለማርያም ተናግረዋል።

## የቀድሞው የኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ዓለማየሁ አቶምሳ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሕወሃት በግንቦት 7 ስም ተከሰው ባሁኑ ሰአት በእስር እየማቀቁ ባሉ ኢትዮያያዊይን ላይ የተጠለፉ የጋደኛ የስልክ ንግግሮችንና የኢሜል መልክቶችን በማገጠተምና በማቅረብ ለክስ ማስረጃነት እንዳቀረበ የሚያስታውሱት ምንጮቻችን የሚጠረጠሩ የወያኔ ባለስልጣናትም በህወሃት ተቀነባብረው በጓደኞቻቸው ስም የተላከላቸውን መልክት እንዲመልሱ በማድረግ ይህንንም በመረጃነት ለመጠቀም ይችላል ይላሉ። ሌሎችን የብአዴንና ደህዴን የወያኔ ከፍተኛ አመራር አባላትም በተመሳሳይ ስለላ ስር እንደሆኑ የጠቆሙት ምንጮቻችን አንዳንዶች ምንም አይነት የቴክኖሎጅ ውጤት ላለመጠቀም እያንገራገሩ ቢሆንም ስራን ለማቀላጠፍና ለማፋጠን ግን የግድ መጠቀም እንዳለባቸው እንደሚናገሩ ጭምር አጋልጠዋል።

# የእሳት ፖለቲካ በኢትዮጵያ

(ይሄይስ አእምሮ - ከኢትዮጵያ)

ከሰሞኑ በሃይማኖት መሪዎችና አገልጋዮች ዙሪያ አንዲት መጣጥፍ ጽፌ እዚሁ አጠገቤ ላሉት የአገር ቤትና ዉጭ አገርም ላሉ ድረ ገፆች ልኬ ነበር፡፡ ለጎሊናቸው ተገዢ የሆኑ አወጡት - አስነበቡን፤ እግዚአብሔር ይስጣቸው፡፡ ለባህልና ለይሉኝታ ያደሩት እንዲሁም እነሱ በሚፈልጉት ሙዚቃ ብቻ ታንጎና ማሪንጌ መደነስ የሚፈልጉት ወደቅርጫታቸው ከተቱት - ይክተቱት፡፡ ዬኔ ተግባር የእዉነት አምለክ ለሁላችንም የልቦናና የሂሊና ሚዛን እንዲሰጠን መፀለይ ነዉና ሁሉም የመሰለውን የማድረግ መብት አለውና ያነበበም ያስነበበም፣ ያፈነም ያሳፈነም የኅሊናው ዳኝነት ይፍረደው ከማለት ውጪ በዚህ በውዥንብር ዘመን መወቃቀሱም ሆነ መካሰሱ ፋይዳ የለውም፡፡ ግን ግን የእውነት አምላክ ለሁላችንም እውነተኛውን የልቦናና የኅሊና ሚዛን እንዲሰጠን እጸልያለሁ፡፡ ሁለትና ሁለት ሲደመር አራት ብቻ የሚሆንበት ሃቀኛ ዘመን ፀሎቴን አላቋርጥም፡፡ ፀሎቴ ሁለትና ሁለት አራት ብቻ የሚመጣበት ሀቀኛ ዘመን እንዲመጣልንም ነዉ፡፡

አንድ ዉጭ አገር የሚኖር ወዳጄ ያቺን ከላይ የጠቀስኳትን በሀይማኖት ላይ የጻፍኳትን መጣጥፍ ካነበበ በኋላ በነካ እጁ በዚህች ወያኔያዊ የእሳት ፖለቲካ ላይ ጥቂት ነገር እንድል አሳሰበኝ፡፡ ርዕሲቱንም የሰጠኝ እርሱ ራሱ ነውና ባለበት ቦታ ምስጋናዬ ይድረሰዉ፡፡ -

ሀገራችን ተመልካች ያጣ የህዝብ ብዛት ብቻ ሣይሆን ጭንቅት የሚያዞሩ እጅግ በርካታ ችግሮች የሚርመሰመሱባት አገር ናት፡፡ አንዳንዴ አንባቢን ላለማስቸገር ወይም ብዙ አንባቢ የለም በሚልና ተነብቦስ ምን ፋይዳ ያመጣል ከሚል ብሶት የተነሣ ሆን ብለን እየተውነው ነዉ እንጂ መጻፍ የምንፈልግ ዜጎች የምንጽፈበት ጉዳይ በሽበሽ ነው፡፡ የወያኔው የዘረኝነት አባዜ ካስከተለብን ተነግሮ የማያልቅ ሰቆቃና የግፍ አስተዳደር ጀምሮ እነሚሚ ስብሃቱን የመሳሰሉ የሥርዓቱ ዘውጋዊ አባላትና እበላ ባይ ሆዳም ደጋፊዎቻቸው ባቋቋሟቸው የሠራተኛ አስቀጣሪ ድርጅቶች አማካይነት የሚካሄደውን ዘመናዊ ባርነት ብንመለከት ጉዳችን በጽሑፍም ሆነ በቃል ተዘርዝሮ የማያልቅ አስገራሚ ፍጡራን ሆነናል - እኛ "ኢትዮጵያውያን"፡፡ ቴዲ አፍሮ "እዚህ ጋ'ም እሳት፣ እዚያ ጋ'ም እሳት፣ እሳት፣ እሳት፣እሳት..." ሲል እንዳቀነቀነው ሀገራችን ወያኔያዊ እቶን ላይ ተጥዳ በየአቅጣጫው እንደባቄላ አሹቅ እየተንገረገበች ናት፡፡ ፖለቲካው እሳት፣ ሃይማኖቱ እሳት፣ ፌዴራሉ እሳት፣ ፖሊሱ እሳት፣ ቀኑና ሣምንቱ እሳት፣ ወሩና ዓመቱ እሳት፣ ኑሮው እሳት፣ ባለሥልጣናቱ እሳት፣ ነጋዴው እሳት፣ ዳኛው እሳት፣ በሽታው እሳት፣ ርሀቡ እሳት፣...፡፡ ሁሉም በእሳት አለንጋ ይጋረፋል፤ ይጠብሳል፤ ይሸነቁጣል፤ የት እንድረስ? የትስ እንግባ? ከነዚህ ከሲዖል ካመለጡ ሽፍቶች የሚታደገን ማን ነው? አምላከ ኢትዮጵያ ወዴት አለ? ኤሎሄ! ኤሎሄ! ኤሎሁም! በዚህ መከራችን ላይ ነው እንግዲህ ወያኔ በሐረርም በአዲስ አበባም እንደዚያች ተዘውትራ እንደሚነገርላትና "እዚህ አካባቢ እሳት ይነሳል ብያለሁ" ብላ ባስጠነቀቀች ማግስት ራሷ እንደምትለኩሰው የደሴዋ ዕብድ ሴት በሹምባሾቹ አማካይነት በሚፈልጋቸው ቦታዎች ላይ እሳት እየለኮሰ፣ እንዳይጠፋም ከልካይ ዘብ እያቆመ በሀገር ሀብትና በሕዝብ ዕንባ እየተዝናና የሚገኘው፡፡ ለማንኛውም አስታዋሼን ላመስግንና በጠቆመኝ ሃሳብ ዙሪያ እንዳመጣብኝ ትንሽ ልብከንከን፡፡ እውነትን ላለማየት ዐይነ ኅሊናቸው የታወረ፣ እውነትን ላለመስማት ዕዝነ ልቦናቸው የተደፈነ፣ አእምሯቸው በፀረ-ለውጥ ቫይረስ ለፈውስ ባስቸገረ ሁኔታ ብልሹ ለሆነ የ"ሚዲያ ሰዎች"ም የቮልቴርን አባባል ባስታውሳቸው ቅር አይለኝም - ቮልቴር እንዲህ አለ አሉ፡- "በምትናገረው ሁሉ ባልስማማም መናገር የምትፈልገውን ጉዳይ በነፃነት መናገር እንድትችል ግን ሕይወቴንም ቢሆን እገብርልሃለሁ!" አይ ኢትዮጵያ! በሁሉም ድሃ፡፡ ግን ተስፋ አለኝ - ትልቅ ተስፋ፡- ወደፊት አንድ ቀን ይህ ሁሉ ድንቁርናችንና ከንቱ ትምክህታችን እንደጤዛ ሲረግፍልን ሰው እንደምንሆን፡፡

በዓለማችን የፖለቲካ ዓይነቶች ብዙ መሆናቸው ከናንተ የተሠወረ አይደለም፡፡ የድንበር ፖለቲካ፣ የውኃ ፖለቲካ፣ የዘር ፖለቲካ፣ የዘውግ ፖለቲካ፣ የውጭ ብድርና ዕርዳታ ፖለቲካ፣ የሀገር ውስጥ የድርቅ ጊዜና የርሀብ ወቅት ዕርዳታ ፖለቲካ፣ የሃይማኖት ፖለቲካ፣ ... ዝርዝሩ ብዙና ኪስን ሳይሆን አንጎልን የሚቀድ ነው፡፡ ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ያልሞከረው የፖለቲካ ዓይነት ደግሞ የለም፡፡ እርግጥ ነው ወያኔ ብቻውን አይደለም፡፡ ይህ ቀረሽ የማይባል ሁለንተናዊ ድጋፍ ለወያኔዎች በገፍ እየሰጡ በ17 ዓመታት ውስጥ የሰው ኃይሉን ከሰባት ሰውነት ወደሚሊዮንነት በማሳደግ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋማቸውን በተግባር የገለጡት የውጭ ጠላቶቻችንም በዚህ ኢትዮጵያን ወደፖለቲካዊ ቤተ ሙከራነት የመለወጡ ሂደት ውስጥ ያሳዩት ጉልህ ተሳትፎም ለአፍታ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ከዓለም ሕዝቦች መካከል እኛ ኢትዮጵያውያን ላይ ያልተፈተሸ ፖለቲካዊ መርዝ የለም፡፡ ባጭሩ የወያኔ ብቻ ሣይሆን የፈረንጆቹም guinea pig ሆነን የቀረን ብቸኛ መዘባበቻ ዜጎች ብንኖር እኛ ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ እርግጥ ነው እነኢራቅንና አፍጋኒስታንን ብንረሳ አግባብ አይደለም - እኛን እየገረፈን ያለው የኃያላኑ የእሳት ወላፈን እነሱንም እየጠበሰ ነውና፡፡ "አልማሊኪ ቡሽ፣ ካርዛይ ቡሽና መለስ ቡሽ እያሉ ሃቀኛ ሰላም አይኖርም፡፡"

ወያኔ ተግባር ላይ ካዋላቸው ሕዝብን የማሰቃያና ሀገርን የማውደሚያ መንገዶች አንደኛው እሳት ነው፡፡ እንዲህ የምላችሁ ወዳጄ አሁን ስላስታወሰኝ ብቻ እንዳይመስላችሁ፡፡ ከጥንትም በሚገባ አውቀዋለሁ፡፡ ለነገሩ ጨካኝና አምባገነን መንግሥታት ለዓላማቸው ስኬት የማያደርጉት ነገር የለም፡፡ ደርግም በተወሰነ ደረጃ ይህን የእሳት ፖለቲካ ይጠቀምበት እንደነበር በጊዜው ሰምቻለሁ፡፡ ሞኙ ደርግ እሳትን ይጠቀምበት የነበረው ኮንትሮባንድን ከመቆጣጠር አንጻርና በጣም በጥንቃቄ እንደነበር በወቅቱ የነበሩ አሁን ድረስ ያስታውሳሉ፡፡ የወያኔ ግን የተለዬ ነው፡፡

በመሠረቱ ወያኔ ምን እንደሆነ መናገር የዐዋጁን በጆሮ ነው፡፡ ይሁንና ወያኔዎች በተጣባቸው የትውልድ መርገምት ምክንያትም ይሁን በሌላ ከሆዳቸውና ያሻቸውን እንዲሠሩ ከሚጠቅማቸው የጨበጡት ሥልጣን በስተቀር የኢትዮጵያዊነት ስሜት በጭራሽ የሌላቸው፣ እንዲያውም ከያዙት ጥቅምና ሥልጣን ያስወግደናል ብለው የሚፈሩት በቀን ሰመመንና በሌት ቅዠት የሚያባትታቸው የኢትዮጵያዊነት ስሜት በመሆኑ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚልን ዜጋ ሁሉ በየሄደበት እያሳደዱና እየገደሉ በደም ባሕር እየዋኙ የሚኖሩ፣ ጥላቻውንም የማያምኑ የከተማ ወሮበሎች መሆናቸውን እዚህም ላይ በድጋሚ ማስታወሱ በአሰልችነት ሊያስወቅስ አይገባም፡፡ እናም አስታውሱ - ወያኔ የዜጎችን የላብ ውጤት የሆነ ሀብትና ንብረታቸውን ማቃጠል ብቻም ሣይሆን ሕዝብን በሠልፍ ኮልኩሎ እንደሂትለር የኦሽትዊዝ ቻምበር የማይፈልጋቸውን በጋዝ እየለበለበ ቢፈጃቸው የሰይጣናዊ ተፈጥሮው የሞራል ምሰሶ ከፋትና ጥፋት ነውና ደስታን የሚያስገኝለት እንጂ ሰብኣዊነት የሚሰማው ሩህሩህ ፍጡር አይደለም፡፡ ሰብኣዊነትና ወያኔ ዐይንና ናጫ ናቸው፡፡

ወያኔዎች እንደገቡ ሰሞን የምንሰማቸው ብዙ የእሳት አደጋዎች ነበሩ፡፡ እነዚያ እሳቶች እንደሰሞነኞቹ የሕዝብን አንጡራ ሀብትና ገንዘብ ለማቃጠል የታለሙ ሣይሆኑ ጫካና ደን የማያውቁት መደዴዎቹ ወያኔዎች ደቡብ ኢትዮጵያንም እንደሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለማራቆት የታቀዱ ደኖችን የማቃጠል ወያኔያዊ የክተት ዘመቻዎች ነበሩ፡፡ በርካታ የደቡብና የኦሮሞ ብሔር መኖሪያ አካባቢዎች በነዚያ ወያኔ በቀሰቀሳቸው የሰደድ እሳቶች ተቃጥለዋል - አንጀታቸው ለተፈጥሮም የሚጨክን አረመኔዎች ናቸው፡፡ በምክንያትነት ሲቀርብ የነበረው ግን የኦነግን ሽማቂዎች ከምንጫቸው ለማድረቅና መደበቂያ ቦታ ለማሳጣት የሚል ነበር፡፡ ትግራይ ውስጥ ወያኔን ሊደብቅ የሚችል ዋሻ ካልሆነ በስተቀር ደንና ጫካ እንዳልነበረ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ጫካ ቢኖር ኖሮ ወያኔን ለማጥፋት በሚል ሰበብ የደርግ መንግሥት ነዳጅ በቦቴ መኪናዎች ጫካ ውስጥ እየደፋ በአብሪ ጥይትም በአሻጋሪ እየለኮሰ ሀገር ለማቃጠል የሚያበቃው የሞራል ድቀት ውስጥ እንዳልነበረ ያንጀቴን እመሰክራለሁ - ሰው ካልሞተ ሚስትም ካልተፈታች ወይ ካልሞተች አይመሰገኑም ወንድማለም፡፡ ደርግ ዜጎችንና ሀገርን በእሳት አይቀጣም፤ ደርግ ኢትዮጵያዊ ጨካኝ እንጂ እንደወያኔ ወፍዘራሽ የባንዳ ውላጅ አልነበረም፡፡ እሳት ባለጌ ነው፡፡ እሳት እጅግ መጥፎ ነው፡፡ ምሕረትን አያውቅም፡፡ እንኳንስ ዜጋህን ጠላትህንም ቢሆን በአግባቡ ውጋው እንጂ፣ በአግባቡ ቅጣው እንጂ ኢ-ሰብኣዊ በሆነ ሁኔታ በእሳት አትገርፈውም፡፡ እነሂትለርና ሙሶሊኒ እንኳንስ ዜጎቻቸውን ጠላቶቻቸውንም ቢሆን በሰደድ እሳት አልቀጡም፤ በእሳት መቅጣት የጀግና ሙያ ሳይሆን የፈሪ ዱላ ነው፡፡ ወያኔ ግን ከየትኛው የጀሃነብ ሰማይ እንደወረደብን አይታወቅም ይሄውና ጫካና ደንን ከማቃጠል አልፎ የምሥኪን ዜጎችን ቤትና ንብረት እንዳሻው በሚያዛቸው ኅሊናቢስ ጀሌዎቹ እያቃጠለ ይገኛል፡፡ ወያኔ እኮ በእሳትም ብቻ ሳይሆን እንደተራ ተንኮለኛ ዜጋ ምግብንና መጠጥን በመመረዝና የታወቀ ጠንቋይ ቤት ድረስም በመሄድ የሚጠላቸውን የሚያስወግድ ጉደኛ ፍጡር ነው፡፡ ኪሮስ አለማየሁ እንዴት ሞተ? አለማየሁ አቶምሳስ? በውነት ቆሻሾች ናቸው፡፡ ምን አድርገን ይሆን ፈጣሪ እነዚህ ለቅጣት የሰጠን ግን? እስኪ ወደዬኅሊና ጓዳችን እንግባና ራሳችንን በቅጡ እንመርምር፡፡

በዚያን ሰሞን ሐረር ውስጥ የተቃጠለው መንደር የዚሁ የወያኔን ዜጎችን በእሳት የመቅጣት የእሳት ፖለቲካ ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያን ገንዘብ ለራሱ ፖለቲካ በመጠቀም ዜጎችን በአነስተኛና ቀጫጭን የሚባል አዲስ ፈሊጥ እያደራጀ አንዱን ርሃብተኛ ሌላውን ጥጋበኛ እያደረገ እናያለን፡፡ በጥቃቅን የማይደራጅን በጠላትነት በመፈረጅ በገቡበት እየገባ ያሳድዳቸዋል፡፡ ከወያኔ የተለዬ ነጋዴ ኑሮውና ግብሩ እሳት ሆነው እንዲያቃጥሉትና ከሀገር እንዲጠፋ ወይም በርሀብ አለንጋ ተገርፎ እንዲሞት ሲደረግ ወያኔን የተጠጋ ሆድ አደር ግን እምብርቱ እስኪገለበጥ እየበላና እየጠጣ ተንደላቅቆ ይኖራል፡፡ እንዲህ እንዲኖርም በመዥገሮች የተወረረችው እናት ሀገር በወያኔዎቹ አማካይነት ለአንዱ የእንጀራ እናት ለሌላው ደግሞ የእውነት እናት ሆና ለሆዳም ጥገኞቹ ሁሉንም ነገር እያመቻቸችላቸው ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ በወያኔ ማኅበር ያልተደራጀ ዜጋ ሁለት በሁለት ለሆነች የንግድ ቤት ከገቢው ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን እጅግ ከፍተኛ ኪራይና ግብር እንዲከፍል ሲገደድ (ሂድ አትበለው እንዲሄድ ግን አድርገው በሚሉት ፈሊጣቸው) ለሆዳሞቹ ግን ካስፈለገ ካለኪራይና ካለአንዳች ግብር በሕዝብ ገንዘብ እንደፈለጉ ይሆናሉ፡፡ ባንኮች ሳይቀሩ ለነሱ የግል ጥገቶች ናቸው፡፡ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ አገር ዉስጥ ያለዉን ኢትዮጵያዊ እያስራበ ዉጭ ያለዉን እየሰለለ የአገሪቱን ገንዘብ እንደሚያባክን ተጋለጠ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት መከበር የሚታገሉትን በዉጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን ለመሰለል በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚያባክን ከየቦታዉ በመደመጥ ለይ ነዉ። በቅርቡ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲና እንግሊዝ ሎንደን ዉስጥ ጉዳያቸዉን ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ኢትዮጵያዉያን ለአለም ህዝብ እንዳሳወቁት ወያኔ በረቀቀ መንገድ የስለላ መረቡን ዘርግቶ ንግግራቸዉንና የኮምፒተር ላይ መራጃቸዉን ለመሰረቅ ተደጋጋሚ ሙከራ እንዳደረገ ለማወቅ ተችሏል። አሁን ከሰሞኑ ደግሞ ሂውማን ራይትስ ዋች ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ የህዝብና የአገር ሀብት እያባከነና እጅግ በጣም የረቀቀ የውጭ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በአገር ውስጥ እና በውጭ የሚኖሩ  ፖለቲከኞችንና ጋዜጠኞችን ይሰልላል ብሏል።

ድርጅቱ ባወጣው ባለ 100 ገጽ ሪፖርት፣ የኢትዮጵያ መንግስት ለስርአቱ አደገኛ ናቸው ብሎ የሚያስባቸውን በውጭና በአገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎችን ለመሰለል ከተለያዩ አገሮች ቴክኖሎጂዎችን ማስገባቱን ” ገልጿል። የመንግስት ድርጊት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ በነጻነት የመደረጃትና መረጃ የማግኘት መብትን እንደሚጥስ የገለጸው ሂውማን ራይትስ ወች፣ መንግስት ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠረው ቴሌኮሚኒኬሽን አማካኝነት የስለላ ስራውን እንደሚሰራ አመልክቷል።
ለኢትዮጵያ መንግስት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚሸጡ ድርጅቶች ፣ መንግስት በህገ ወጥ መንገድ ለሚያደርገው ስለላ ድጋፍ እየሰጡ ነው” በማለት የድርጅቱ የቢዝነስና የሰብአዊ መብቶች ዳይሬክተር የሆኑት አርቪድ ጋንሲያን ተናግረዋል።

ሪፖርቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እንዲሁም የቀድሞ የደህንነት ሰራተኞችን በማነጋገር የተጠናቀረ ነው፤፡መንግስት በወንጀል የጠረጠራቸውን ሰዎች አስሮ በሚያሰቃይበት ጊዜ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የጠለፋቸውን ስልኮች በማስረጃነት አቅርቦ እንደሚያሰማ እንዲሁም ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፎች በሚደረጉበት ጊዜ የስልክ መስመር ( ኔት ወርክ) እንደሚጠፋ ድርጀቱ በሪፖርቱ አመልክቷል። ለስለላ ተግባር የሚውሉት አብዛኞቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከቻይናው ዜቲኢ መገኘቱን ሪፖርት፣አመልክቷል፡፡ እንዲሁም ተቀማጭነቱን በዩናይትድ ኪንግደምና በጀርመን ካደረገው ጋማ ኢንተርናሽናል ፊን ፊሸርን፣ ከጣሊያኑ ሃኪንግ ቲም ከርቀት ለመቆጣጠር የሚያስችል መሳሪያ አግኝታለች።

## የሻኪሶ ህዝብ በአካባቢዉ ለተነሳዉ  ብጥብጥ ከወያኔ ዉጭ ሌላ ተጠያቂ የለም አለ

በወርቅ ማዕድኗ በታወቀችዉ ሻኪሶ ዉስጥ ከአስር ቀናት በፊት ጎሳና ቋንቋን ማእከል አድርጎ በተማሪዎች መካከል በተነሳው ብጥብጥ ዉስጥ የከፍተኛዎቹ የወያኔ ባለስልጣናት እጅ አለበት ሲሉ የከተማዋ ነዋሪዎች ተናገሩ። ሻኪሶ ዉስጥም ሆነ በአካባቢዋ በሚገኙ ከተማዎች ዉስጥ ተማሪዎች ለብዙ አመታት ጎን ለጎን ተቀምጠዉ በሰለም የተማሩ ሲሆን ባለፈዉ ሰሞን የታየዉ ብጥብጥ እንዲነሳ ሁኔታዎችን ያመቻቹት የወያኔ ባለስልጣኖች መሆናቸዉን ህዝቡ በማገር ላይ ነዉ።  የከተማው ባለስልጣናት በግጭቱ ዙሪያ ህዝቡን በማወያየት ላይ ሲሆኑ፣ የከተማው ነዋሪዎች በተደጋጋሚ ለሚነሳው ግጭት የአካባቢው አስተዳዳሪዎች እጅ አለበት ማለታቸውን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ አንድ የከተማዋ ነዋሪ ለኢሳት ገልጸዋል።

በዚህ ሳምንት ሻኪሶ መረጋጋት ቢታይባትም ተመሳሳይ ችግር ሊከሰት ይችላል የሚል ፍርሃት መኖሩን ከአካባቢዉ የሚደርሱን ዜናዎች ያመለክታሉ። መጋቢት5 እና 6 ቀን 2006 ዓም በሁለተኛ ደረጃ እና በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች መካከል ጎሳን ማእከል ያደረገ ብጥብጥ ተከስቶ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፣ የብዙ ነጋዴዎች ህንጻዎችም መስታውቶቻቸው ተሰባብሯል። ሃሙስ መጋቢት 6 በዋለው የከተማው ታላቅ ገበያ ላይ በተፈጠረ ሁከት በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት መውደሙን ነዋሪዎች ይናገራሉ። አንዲት ነዋሪ በጽኑ ቆስላ ህክምና ተደርጎላት መመለሱዋን እና በግጭቱ የሞተ ሰው አለመኖሩን ነዋሪዎች አክለው ገልጸዋል። እስካሁን ድረስ በቁጥጥር ስር የዋሉ 12 ሰዎች አለመፈታታቸውም ታውቋል።

## በቅርቡ ከሳዑዲ የተመሰሉ ኢትዮጵያውያን ሁለተኛዉን ዙር ስደት ተያይዘዉታል

ከሁለት ወር በፊት ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ የደረሰባቸዉን ሰቆቃ አምልጠዉ አገራችን ብለዉ ወደ ኢትዮጵያ የተለመሱት አያሌ ኢትዮጵያዉያን አሁን ደግሞ በገዛ አገራቸዉ ከሚደርስባቸዉ ግፍና መከራ ለማምለጥ ጥለዉት ወደመጡት የስደት አለም በመመለስ ላይ መሆናቸዉን አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ።  በሁመራ በኩል ኢትዮጵያን እየለቀቁ ሱዳን የገቡት ብዙዎቹ ኢትዮጵያዉያን ስደተኞች እንደሚናገሩት ለሁለተኛ ዙር ስደት የዳረጋቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስራ አለማግኘታቸዉ ብቻ ሳይሆን ስራ ሲፈልጉ የሚገጥማቸዉ የዘረኝነት አሰራር፤ ወገንተኝነት፤ መብት ረገጣዉና ባጠቃላይ የነጻነት መጥፋት እንደሆነ ተናግረዋል።

በተለይ ወደ ትግራይና አማራ ክልሎች እንዲሄዱ የተደረጉ ስደተኞች በሁመራ በኩል ወደ ሱዳን በብዛት እየጎረፉ መሆኑን የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ።አንዳንድ ወጣቶች ከሳውድ አረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ለቀን ወደ አገራችን ብንገባም በአገራችን የምናየው ነገርም ለስራ የማያበረታታ ነው በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ። ከ130 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን ከሳውድ አረቢያ እንዲወጡ መደረጉ ይታወሳል። መንግስት በአነስተኛ እና ጥቃቅን እንደሚያደረጃቸው ቃል ቢገባም እስካሁን ይህ ነው የሚባል ውጤት አልተገኘም።

## ወያኔ ሕዝባዊ ተቋማትን በድጋሚ የማፈራረስ እቅዱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በ1997 ምርጫ ወቅት ከከተማ ውጭ በነበሩት የኢትዮጵያ አካባቢዎች ፋሽስት ወያኔ እንዲወድቅ ከፍተኛውን ስራ ሰርቷል በመባል በሕወሃት የሚከሰሰው ማህበረ ቅዱሳን የተሰኘው ተቋም፤ ከዚያ ጊዜ ወዲህ በመጀመሪያ በቅንጅት ደጋፊነት ቀጥሎም በትምክህተኞች ጎሬነት አሁን አሁን ደግሞ በአክራሪነት በሚሳበቡ ክሶች ከሕወሃት አይነ ቁራኛነት እንዳልራቀ የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። በሚቀጥለው አመት ይደረጋል ተብሎ ለሚጠበቀው ሀገራዊ ምርጫ እጅግ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የገባው ሕወሃት ይህ ማህበር የጠራ እንቅስቃሴ በማያደርግበት ደረጃ ላይ ማውረድ ተቀዳሚ ዓላማው እንደሆነም ምንጮቻችን ጨምረው ይገልጻሉ። ማህበሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሕወሃትም ሆነ ከሕወሃት ደጋፊዎች ለሚነዛበት አፍራሽ እንቅስቃሴ በተደጋጋሚ በማስረጃ ለመነጋገር ፈቃደኛ እንደነበርና አገዛዙ ግን ያን እንዳልፈለገ የሚጠቁሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ”ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ዥግራ ናት ይሏትል” እንዳይሆን ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

ሕወሃት አገዛዙን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ ለቁጥር የሚያታክቱ የማህበረ ረድኤት፣ የሙያ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊና የፆታ ተቋማትን ከቻለ ገልብጦ ለራሱ አገልግሎት በማዋል ካልሆነ ደግሞ ባንዱ ወይም በሌላ እያመካኘ እንዳጠፋቸው የሚጠቁሙት ምንጮቻችን፤ እንደኛ እይታ ከሆነ የማሕበረ ቅዱሳን ጉዳይ ያበቃለት ይመስላል ይላሉ።

ከዚህ በፊት በተመሳሳይ እርምጃዎች ህወሃት መራሹ ጎታች ቡድን የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርን፣ የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜተኞች ማህበርንና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤን ጨምሮ ሌሎችንም እጅግ ብዙ ሃይማኖታዊ፣ ሕዝባዊና የሙያ ማህበራትን አፋኝ ህጎችን በማውጣትና አክራሪነትንና ሌሎችንም ተልካሻ ምክንያቶች በመደርደር ከጫወታ ሜዳ እንዳስወጣቸው አይዘነጋም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB  በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz
በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz
ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ከፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ሀረር ዉስጥ የደረሰዉ ቀዉስ ወደ ብሄር ግጭት ያመራል የሚል ፍርሀት መኖሩ ታወቀ

ሐረር ዉስጥ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የንግድ ቤቶች መቃጠላቸውን ተከትሎ የተነሳዉ ዉዝግብ በቃጠሎዉ በተጠቃዉ ህዝብና ክልሉን በሚመራው የሃረሪ ሊግ መካከል ከፍተና ቅራኔ መፍጠሩንና ቅራኔዉ በአስቸኳይ ጤናማ መፍትሄ ካላገኘ ችግሩ እየሰፋ ሄዶ በተለያዩ ብሄሮች መካከል ግጭት ሊያስነሳ ይችላል የሚለዉ ፍራቻ ሀረርንና አካባቢዋን እያንቀጠቀጠ መሆኑ በመነገር ላይ ነዉ። ክልሉን የሚያስተዳድረው የሃረሪ ሊግ ” መጤዎች ከከተማችን ውጡ” የሚሉ ቅስቀሳዎችን ከጀርባ ሆኖ በማሰራጨትና የንግድ ቤቶችን በማቃጠል ለዘመናት ተከባብሮና ተቻችሎ የኖረውን የሃረርን ህዝብ በመከፋፈል የብሄር ግጭት ለማስነሳት እየጣረ ነው። እነዚሁ ባለስልጣናት ለህዝቡ ያሰቡ በማስመሰል የሚያሰራጩት ቅስቀሳ፣ በተለያዩ የከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ፍርሃትና አለመረጋጋት እየፈጠረ መሆኑን ነዋሪዎች ይገልጻሉ።

የካቲት 30 ቀን፣ 2006 ዓም በሸዋ በር የንግድ ማዕከል የተነሳውን እሳት ተከትሎ ህዝቡ ሲያሰማው የነበረው መፈክር ፣ በክልሉ ውስጥ ያለውን አለመረጋጋት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ነዋሪዎች ተናግረዋል። በህዝቡ ቁጣ የተደናገጠው አስተዳደሩ በተለያዩ የወረዳ እስር ቤቶች ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን አስሮ እያሰቃየ መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች ለኢሳት ገልጸዋል። አስተዳደሩ መጀመሪያው ቃጠሎ የተነሳው ሳባ በምትባል ሰው ምግብ ቤት ውስጥ ነው በሚል ሳባ የተባለችውን ሰው አስሮ መግለጫ በሰጠ በሳምንቱ በመብራት ሃይል የንግድ ማእከል በድጋሜ ቃጠሎ የተነሳ ሲሆን፣ ሁለተኛው ቃጠሎ የተነሳው በኤሌክትሪክ ችግር ነው በሚል የ ሀረሪ መብራት ሃይል የቴክኒክና ስልጠና ሃላፊ የሆኑትን አቶ ገብሬ ቶላን ጨምሮ ሙላቱ ብዙ፣ ሀይሉ ክንፈና አቡሽ የተባሉ የድርጅቱ ሰራተኞች እንዲታሰሩ ተደርጓል።

መስተዳድሩ ሳይውል ሳያድር ድርጊቱ የሽብርተኞችና በከተማዋ ውስጥ አለመረጋጋት እንዲፈጠር የሚሰሩ ሃይሎች ያስነሱት ነው በሚል በመስተዳድሩ ምክትል ፕሬዚዳንት በኩል መግለጫ መስጠቱ ህዝቡን ይበልጥ ግራ ማጋባቱንና ከቃጠሎው ጀርባ መስተዳድሩ አለበት የሚለውን ጥርጣሬ ከፍ አድርጎታል። መስተዳድሩ በስም ያልጠቀሳቸውን አሸባሪዎች ለማውገዝ ዛሬ በጠራው ሰልፍ በግዳጅ ከወጡት የመንግስት ሰራተኞችና ከገጠር በአይሱዙ መኪኖች ተጭነው ከመጡት ሰዎች በስተቀር አብዛኛው የከተማው ነዋሪ በሰልፉ ላይ ሳይገኝ ቀርቷል። ትናንት ምሽት ጀጎል እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ህዝቡ በሰልፉ ላይ እንዳይገኝና በመንግስት ማደናገሪያ እንዳይታለል የሚቀሰቅስ በራሪ ወረቀት ሲበተን አምሽቷል። እንዲሁም የመንግስት ሰራተኞች በግዳጅ እንዲሰበሰቡ ተደርጎ በቃጠለው ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ገንዘብ እንዲያዋጡ እንዲሁም መንግስት እሳቱን ሆን ብሎ አላስነሳውም ብለው እንዲመሰክሩ እንዲሁም ክልሉ የሚሰራው ለአንድ ብሄር ሰዎች ነው እየተባለ የሚባለው ትክክል አለመሆኑን መስክሩ ተብሎ እንደተነገራቸው ለማወቅ ተችሎአል።

## የእሳት ፖለቲካ በኢትዮጵያ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የሀገር ስሜት ዛሬ ያልጠፋ ታዲያ መቼ ይጥፋ?

ይህ መሰሉና ሌላው ግፍ ሁሉ አልበቃ ብሎ ነው እንግዲህ የእሳቱ ፖለቲካ በሀገር ደረጃ እየተፋፋመ የሚገኘው፡፡ እንደሰማነው በሐረር ከአንዴም ሁለት ጊዜ ቃጠሎ ተነስቶ በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ብርና ሀብትና ንብረት ወድሟል፡፡ ይህ የሆነው በወያኔው ፈቃድና ይሁንታ መሆኑን የምንረዳበት መንገድ ደግሞ እሳቱን ለማጥፋት ጥረት ሲደረግ አስቀድሞ የተዘጋጀው የወያኔ ጦር እሳቱን ከብቦ አላሰቀርብም ማለቱና የእሳት አደጋ ሠራተኞችም እሳቱ የሚፈለገውን ጥፋት ካገባደደ በኋላ ሥራቸውን እንዲሠሩ መፈቀዱ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ግፍ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረግ አይመስለኝም፤ እንዲያውም አይደረግም፡፡ ምክንያቱም የሀገር ዜግነቱን የካደና ሀገር እየቸረቸረ የሚሸጥ የሀገር መሪ ከኢትዮጵያ ውጪ በየትም ሥፍራ ይኖራል ብዬ አላምንምና፡፡

የሐረሩ እሳት መንስኤው ወያኔ ሆኖ ዓላማው ደግሞ ቦታውን ለወያኔያዊ ባለሀብቶች ለመስጠትና በእግረ መንገድም ተቀናቃኝ ኢ-ወያኔያዊ ባለሀብቶችን ለማክሰም ነው - ይህን እውነት ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አያስፈልግም፡፡ በጣም ግልጽ ነው፡፡ መንታ ዓላማ  ያነገበ ቃጠሎ ነበር ማለት ነው፡፡ አንደኛውና ዋነኛው በሥርዓቱ የማይፈለጉ ዜጎችን ማደኸት - ሁለተኛው በነሱ ቦታ ደግሞ ለሥርዓቱ ዕድሜ ቀን ከሌት ተንበርክከው ሰይጣንን የሚለምኑ ፍቁራን አባላትንና ደጋፊዎችን ማቋቋም፤ በቃ፡፡ በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ ይባላል፡፡ በኢትዮጵያ መሬት፣ በኢትዮጵያውያን ሀብትና ንብረት ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑ የመንግሥትን ሞሰብ ገልባጮችና ደጋፊዎቻቸው ይገባበዙበታል፤ ይጠቃቀሙበታል፡፡ እንግዴ ልጅ ሀገር ሻጭ ማዕዱን ሲጫወትበት ልጅ ከበይ ተመልካችነትም ወርዶ የሥቃይ ሰለባ ሆኗል፡፡ እየተራቡ በሀገር መኖርም ክልክል ሆኖ ለሞትና ለስደት መዳረግ ዕጣችን እንዲሆን ተፈርዶብናል፡፡ ይህን ቅሚያና ዘረፋ፣ ይህን የግፎች ሁሉ የበላይ የሆነ ግፍ በእሳት አማካይነት እውን ለማድረግ ደግሞ የኢትዮጵያን መለዮ ለባሽ ይጠቀማሉ -በዓይነቱ ልዩ የሆነ የታሪክ ምፀት ማለት ይህ ነው፡፡ ዋ እኔን! ይህች ቀን ልታልፍ እምቢልታው ሲነፋ እነዚህ ጉግማንጉጎች ምን ይውጣቸው ይሆን?

አዲስ አበባም ውስጥ በትንሹ ሁለት ያህል ቃጠሎዎች በነዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ ተከስተዋል፡፡ አንደኛው የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሲሆን ሌላኛው በአንድ ግለሰብ ቤት የደረሰና የሦስት ሰዎችን ሕይወት የጠየቀ ቃጠሎ ነው፡፡ ያሳዝናል፡፡ ነፍሳቸውን ይማር፡፡ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤቱ ግን ያጠያይቃል፡፡ እርግጥ ነው - ቃጠሎው ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደማንኛውም አደጋ ሆን ተብሎ ሳይሆን ድንገት ሊነሳ የመቻሉ ዕድል እንዳለ ሆኖ ከወያኔ ባሕርይ ተነስተን ስንገምት መነሾው ፖለቲካዊ አንድምታም ሊኖረው እንደሚችል ብንጠረጥር “ጠርጣሪዎች(skeptics)” ተብለን ልንታማ አይገባም፡፡ እንዲያውም ስንትና ስንት ጥበቃ የሚደረግለት ትልቅ ድርጅት በቀላሉ ለእሳት ይዳረጋል ብሎ ከማሰብ አለማሰብ ይሻላል ብለን ብንከራከር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም ከድንገቴ አደጋነት ይልቅ የወያኔው ተንኮል እንደሚኖርበት መገመት አይከብድም፡፡ ወያኔ ለምን ብርሃንና ሰላምን ያቃጥላል? ምን ያገኛል? ከመገመት ባለፈ እውነተኛውን ነገር ማወቅ ሊከብድ ይችላል፤ መገመት ደግሞ ለማንም የማይከለከል የሁሉም መብት ነው፡፡

ከሁሉም በፊት ግን አንድ አጠቃላይ እውነት መኖሩን እንመን፡፡ ያም እውነት ወያኔ ቢቻል ቢቻል ኢትዮጵያ እንዳለች ብትቃጠል ወይም እንጦርጦስ ብትወርድ ደስ ይለዋል እንጂ የማይከፋ መሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ስሟ ሲነሳ የሚዘገንናቸውና ጠበል በመጠመቅ ያለ ሰው ላይ እንደተከሰተ ሰይጣን የሚያንዘረዝራቸው እነበረከትንና ሣሞራን የመሳሰሉ መፃጉዕ ዜጎች የሚገኙበት መንግሥታዊ መዋቅር የኢትዮጵያ ታሪክ የሚዘከርበትና አእምሯዊ ቅርስ የሚቀመጥበት ማዕከል ቢቃጠል አይደሰትም ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ በዕንቆቅልሽ ሀገር ውስጥ ልንጠብቅ የማይገባንን ነገር ብንጠብቅ ብልህነት እንጂ ትዝብት ውስጥ ሊያስገባን የሚችል ሞኝነት አይደለም፡፡

በመሆኑም ወያኔ ይህን የእሳት ፖለቲካውን በመጠቀም ዜጎችን ራቁታቸውን ማስቀረቱንና ወደበረንዳ ሕይወት መለወጡን እንዲያቆም፣ የዘመናት ቅርሳችንን እያቃጠለ ታሪክ አልባ ሆነን እንድንቀር ማድረጉን እንዲገታና እስከተቻለ ደግሞ ነፃነታችንን እውን ለማድረግ የምንችልበትን የጋራ ሥልት መቀየስ እንድንችል የጋራ ጥረት እንድናደርግ ጥሪየን አቀርባለሁ፡፡ ሰላም፡፡